<u>የፓል ቶከ ፉከቻ</u>

ጉደ አንድ ሰሞን

ወንበር መቀመጫ መስኮት መመልከቻ
የዘንድሮ ዘፈን ቆይ ብቻ ፀጥ ብቻ፡፡
የጌቶቹ ምላጭ ኪይ ቦርዱ ሆነና
ጥይቱም አበባ ለበጣ ምስጋና
ቅዕል ስም አንግቦ አትንኩኝ ባይ ጀግና
ዛሬም እንዳለፈው ገዳይ ንፁሃንን
ዛሬም እንደ ትላንት አድናቂ ሽብርን፡፡
ሀጢያት ሰሪ እርጉም መቼ ሜዳ ውሎ
ከማን ጋር ተዋግቶ
በፓል ቶክ ዘመቻ ሁሉን ረፍርፎ፡፡
ቋራ በኢኢዴን ፓልቶክ ለአርማጭሆ
ሁሉም ተተክቶ
መሳለቂያ ሆንን በወያኔ መንጋ
ትግሉም ተረስቶ ወሬ ስድብ ብቻ
መጋረጃው የባዕድ ፓልቶክ መደበቂያ
ፋኖነት ልፈፋ ታጋይ ማብጠልጠሊያ
ያብቃ ይህ አጉል ቀልድ በሕዝብ መሳለቁ
ልፋፊው ይዘጋ ይነገር ያ ሀቁ፡፡
ትግል በኢኢዴን በፓልቶክ ልፈፋ
ለሀገር ሳይጠቅም ያብቃ ይኸ ጉንጭን አልፋ፡፡